# የምን 2.4 ብቻ

ከማተቤ፡ መለሰ፡ ተሰማ

የ1999 ዓ/ም፡ የኢትዮጵያ፡ ሕዝብ ቆጠራ፡ ውጤትን አሥመልክቶ፡ ከሰሞኑ፡ ሪፖርተር ጋዜጣ፡ በሞትና በስደት፡ ምክናያት፡ የአማራው፡ ሕዝብ፡ ቁጥር በ2.4 ቀንሶ፡ እንደተገኜ፡ በመዘገብ አሥነብቦናል፡ በበኩሌ ግን ከዚህ በላይ ሕዝብ አልቋል ባይነኝ፡ ወያኔ ሐገራችንን፡ ከወረረበት፡ ቀን ጀምሮ በዚህ ብሔረሰብ ላይ ያወረደውን፡ ማአት ፡ ወደኋላ ፡ መለሥ፡ ብለን በአይነህሌናችን፡ በጥሞና፡ እንቃኜው፡ እሥቲ!!!

1ኛ/ ወያኔ፡ ለአማራው፡ ብሔረሰብ፡ ነፍጠኛ፡ የሚል ታቤላ በመለጥፍና፡ ነፍጥኛ ማለት ድግሞ፡ ሲገድል፡ ሲዘርፍና፡ ሲገፍ፡ የኖረ በማስመሰል፡ ከእራሱ ከአማራው፡ ወጣን፡ በሚሉ፡ እንደ ታምራት፡ ላይኔ አይነት፡ ካሃዲ፣ ባንዳና፣ ነፍሰ ገዳዮች፡ አማካኝነት፡ መቀስቀስ፡ ብቻ ሣይሆን፡ ሌላው ብሔረሰብ ፡ በመላው ኢትዮጵያ፡ ተበትኖ ይኖር የነበረውን፡ አማረኛ ተናጋሬ በሙሉ፡ ያለምንም ሰባዊ፡ ርህራሔ እንዲጨፈጭፈው፡ ቀጥተኛ፡ ትዕዛዝ፡ በመሥጠት፡ በወለጋ፣ በአሶሳ፣ በጅማ፣ በአርሴና በባሌ፣ በሀረርጌ፡ ወ.ዘ.ተ. በፋሥ የተፈለጠውን፣ በካራ የታረደውን፣ እንደገለባ፡ በአንድቤት፡ ተሰብሥቦ፡ ተዘግቶበት፡ በእሣት የተቃጠለውን፣ ከእነህይወቱ፡ በገደል፡ የተወረወረውን፡ በመትርየስ ይታጨደውንና፡ ዛሬም ሌላ ምንም ሀጢያት፡ ሣይሰራ አማረኛ ቋንቋን፡ በመናገሩ ብቻ፡ በእየቦታው እንደዱር፡ አራዊት፡ እየታደነ፡ በመገደል ላይ ያለውን፡ አማራ፡ ብንደምረው፡ ከ2.4 በላይ አይሆንምና፡ ነውን?

2ኛ/ ክልልህ ነው፡ በሚለው፡ የሚኖረውን ሕዝብ፡ ደጋፊውን፡ ጭቁን፡ ይቃወመኛል ብሎ ፡ የሚገምተውን፡ ጨቋኝ፣ ትምክትኛ፣ ቢሮክራት፡ እያለ፡ በመከፋፈል፡ ሲፈልግ እንደ መምህራን ማህበሩ፡ አበራ ማኑ፡ እንደጎጃሙ አርሶ አደር ምናሉ፡ መንገሻ፡ በጠራራ ጸሀይ፡ በጥይት፡ በመረሸን፡ ሲፈልግ ሰሜን ሸዋ፡ አስተዳድር፡ ጽ/ቤት ይሰራ እንደነበረው፡ ሽመልስ፡ አረጋና እንደ ንግድና ኢንዱስትሬ፡ ሚኒስቴር፡ ዔክስፔርቱ፡ ሙሉየ፡ ሽፈራው፡ ወ.ዘ.ተ. አፍኖ ድራሹን በማጥፋት፡ የፈጀው፡ የአማራ ህዝብ፡ ቢደመር ከ 2.4 በላይ አይሆንምና ነውን?

3ኛ/ ወያኔ ለዘቀጠው፡ የጎሣ ፖለቲካው፡ ታዳሚ አልሆንም፡ ያለውን የአማራ ክልል፡ አርሶም ይሁን ነግዶ አዳሬ፡ በተለያዮ፡ የውሸት ወንጀሎች፡ እያዋከበ ቤት ንብረቱን፣ መሬቱን በመዝረፍ፡ ከቅየው ሥለአፈናቀለው፡ ጥሎ የተሰደደውን፡ ለብቻው፡ ከሞተው፡ ለይተን፡ ብንደምረው፡ ከ2.4 በላይ አይሆንምና ነውን?

4ኛ/ ወያኔዎች፡ በአማራው፡ ህዝብ ላይ ከከፈቱት፡ መጠነሰፊ፡ የሥነ ተፈጥሮ፡ ጦርነት፡ ወይንም የረቀቀ ዘር ማጥፋት፡ ዘመቻ፡ ውስጥ፡ አንዱን፡ ብቻ እንኳን፡ ብንጠቅስ በሌላው ክልል፡ ሥራላይ፡ ሊውል ቀርቶ፡ በጭራሽ ያልታሰበውን፡ በወሊድ ቁጥጥር፡ ሰበብ ቀስበቀስ፡ የአማራውን ዘር ለማጥፋት ሲባል፡ ወልዶ እንዳይተካ፡ አርሶ አደሩን፡ እሽ ያለውን በገንዘብ፡ በማባበል፡ እንቢ ያለውን፡ ቤትህን እናፈርሣለን፡ ንብረትህን እንወርሣለን፡ በማለት እያስፈራሩ፡ የዘር ብልቱን፡ እያኮላሹት፡ ከበሆናቸውም፡ በላይ፡ የወባ፣ የሣንባ፣ የውሃ ወለድ፣ የዔች አይቢ፡ በሽታውች፡ በሰው ሰራሽ መንገድ ተራብተው፡ በአማራው ክልል፡ የመጨረሻውን፡ እርከን እንዲርግጡ፡ ተድርጓል፡ እያንዳንዳቸውን፡ መዘርዘሩ፡ ያንባብያንን፡ ጊዜ ያባክንብኛል፡ ብየ ስለምስጋ፡ ልለፍና፡ እስኪ ለአብነት፡ የወባ በሽታን፡ በተመለከተ፡ ከዕውነታው፡ እውቅያኖስ፡ ጨለፍ አድርጌ፡ ልግለጽ!!!

4.1. የወባ በሽታ፡ ድሮ የሚከሰተው፡ በቆላማ አካባቢዎች፡ ብቻ ሲሆን ከበዛም፡ አልፎ አልፎ፡ ወይና ደጋ፡ ወደሚባሉት፡ የሚታይበት ጊዜ፡ ቢኖርም፡ ከወያኔ በፊት የነበሩ፡ መንግስታት፡ በሽታው፡ ይከሰትባቸዋል፡ ተብለው፡ በሚገመቱ፡ ቦታዎች፡ የወባ መቆጣጠሪያ፡ ጣቢያዎችን፡ በማቋቋምና፡ ፍቱን መዳህኒት በማቀረ፣ እንዲሁም፡ በሙያው የተካነ፡ በቂ የሰው ሃይል ተመድቦ፡ በአመት፡ 2ና 3 ጊዜ፡ እርጭት ይካሄድ ሥለነበር፡ ጨርሶ ማጥፋት ባይቻልም፡ እንኳን ብዙ ሰው አይሞትም ነበር፡ በፋሽሰቱ በወያኔ፡ ዘመን የተደረገው፡ ግን በጣም በሚያሥገርም፡ ሁኔታ በተገላቢጦሽ ነው፡ ወያኔ፡ በአማራ ክልል፡ በተለይም በምዕራብ፡ ጎጃም ዞን፡ ደጋ በሚባለው፡ አካባቢ ሣይቀር፡ በተራቀቀ፡ የሣይንሥ፡ ውጤት፡ የተፈበረከ፡ በሽታውን፡ የሚያጠፉ፡ ሣይሆን የሚያፋፋና፡ የበለጠ፡ የሚያራባ፡ ምንም አይነት ፡ መዳህኒት የማይገድለው፡ ምንም አይነት የአየር ንብረት

የማይበግረው፡ የሚያደርግ፡ ልዩ፡ መዳህኒት፡  ካሥረጨ፡ በኋላ ለረጅም ዘመናት፡ አገልግሎት፡ ሲሰጡ የኖሩትን፡ የወባ መከላከያ፡ ጣቢያዎች፡ በመዝጋት፡ በተለይ ደጋዳሞት፣ ቋሪት፣ ጃቢጠህናን፣ ደንበጫ፣ ቡሬሽኩዳድ፣ ዳጉሣ በንበርማ፣ ሥከላ፣ በተባሉ 7 ወረዳዎች የሚኖረው ህዝብ፡ ከ1984 ዓ/ም  ጀምሮ፡ እንደቅጠል ሲረግፍና፡ በአንድ ቀን 10 ና15 ሰው ከአንድ ቀበሌ ሲሞትና፡ ቀባሪ ጠፍቶ፡ ያለባህሉ፡ አስከሬን፡ አፈር ሣይለብሥ፡ ለቀናቶች፡ ቤት ውሥጥ፡ ሲቀመጥ፡ የወያኔ፡ ባለሥልጣናት፡ ዝምብለው ማየት ብቻ ሣይሆን፡ በአካባቢው፡ ምንም አይነት የህክምና፡ እርዳታ፡ እንዳይደርሥ፡ አጥብቀው፡ ይከላከሉ፡ እንደነበር፡  እኔ የአይን ምሥክር ነኝ፡ እንዴትእነቱን፡ ልናገር፡ እልቂቱ፡ በጀመረ፡ በሁለት አመቱ፡ 1986 ዓ/ም ጥር ወር ላይ 10 ቀን የፈጀ፡ የአማራ ክልል፡ ባለሀብቶች፡ የተሣተፉበት፡ ስብሰባ፡ ባህርዳር፡ ከተማ ላይ ይካሄድ ሥለነበር፡ እኔም ከተሰብሣቢዎቹ፡ አንዱ ነበርሁና፡ የተወሰን ሰዎች ተነጋግረን፡ የክልሉ መንግሥት፡ ከያዘው፡ የመወያያ አጀንዳ፡ ጣልቃ በማስገባት፡ በሀሣብ ደርጃ፡ ወገናችን በወባ በሽታ፡ እያለቀ ሥለሆነ፡ እኛ፡ ገንዘብ በማዋጣት፡ መዳህኒት ገዝተን እናድል፡ የሚል ሀሳብ ብናቀርብ፡ በእረፍት ጊዜ በውቅቱ፡ የክልሉ፡  መንግስት፡ፕሪዝዳንት : የነበሩት አቶ አዲሱ ለገሰ፡ አሥጠርተው፡ ይህንን ሃሣብ ደግመን፡ እንዳናነሣ፡ ማስጠንቀቂያ፡ ስለሰጡን፡ ውሾን ያነሣ፡ ሆኖ ቀርቷል። ያሣያችሁ፡ እንግዴህ ውድ አንባብያን፡ 2 አመት ሙሉ፡ ያሁሉ፡ ህዝብ አልቆም፡ ገና የልባቸው፡ አልደረሰም ነበር፡ እናም፡ በዚህ ፍጹም አረመኔያዊ፡ ወያኔ ሰራሽ፡ የወባ ወረርሽኝ፡ ብቻ በአማራው፡ ክልል ያለቀውን፡ ሕዝብ ብንደምረው፡ 2.4 በላይ አይሆንምና ነውን? ዛሬ በእየክልሉ፡ ከተገደለውና፡ ከተሰደደው፡ ጋር ተደምሮ፡2.4 ብቻ ነው፡ የሚባለው? በሰው ቁሥል እንጨት ቢሰድዱበት፡ አያምም ይሏል እንደዚህ፡ ነው።

 ከብዙ እልቂት፡ በኋላ ግን ከአማራ ክልል ውጭ፡ የሚኖሩ የአካባቢው፡ ተወላጆች፡ ባደረጉ፡ ከፍተኛ ጥረት፡ በሽታው፡ ሊገታ በመቻሉ፡ በአጠቃላይ፡ ለዚህ፡ ነፍሣድን ጥሬ፡ ጀሮአቸውን፡ በመስጠት፡        የጊዜ፣ የገንዘብ፣ የአዕምሮና፣ የጉልበት፡ መሷዕትነትን፡ ከፍለው፡ የወገናቸውን፡ ህይወት፡ የታደጉትን፡ በተለይ፡ ደግሞ፡ አስተባባሪ፡ ኮሚቴውን፡ በዚህ አጋጣሚ፡ ላመስግናቸው፡ እፈልጋለሁ፡ መሰናከሉ፡ ቀላል፡ እንደማይሆን፡ ስለምረዳ።

 ወያኔ የአማራውን፡ ዘር ለማጥፋት፡ ያካሔደውና፡ አሁንም፡ የሚያካሂደው፡ እጅግ በጣም፡ የረቀቀ ዘመቻ፡ ይህ ብቻ አይደለም፡ ይቃዎሙኝ ይሆናል፡ ብሎ የሚገምታቸውን፡ የአማራ፡ ተወላጆች፡ ከሣሽም፣ መርማሬም፣ አቃቢህግም፣ ምስክርም፣ ዳኛም፡ እራሱ፡ ሆኖ በተለመደው፡የሀሰት፡ ውንጀላው፡ እስርቤት፡ ያሥገባና በምግብ፣ በመጠጥ፣ በህክምና፡ ወ.ዘ.ተ. ገዳይ ቫይረሶችን፡ እየሰጠ ፈጅቷል፡ አሁንም እየፈጀ ነው፡ በዚህ ሁኔታ፡ እስር ቤት ያለቀውንና፡ እንደተመረዘ፡ ሲታወቅ፡ ከእሥር እየተለቀቀ፡  እንደወጣ የሞተውን፡ የአማራ ህዝብ፡ ቤቱ ይቁጠረው፡ ማለቱ በቂ ቢሆንም፡ ለአብነት፡ እንጥቀሥ ከተባለ፡ 1/ ፐ/ር አሥራት ወ/ እየስን፡ 2/ የሰሜን ሸዋ ዋና አሥተዳዳሪ፡ የነበሩትን፡ አቶ ጌታቸው አበበን፡ 3/ የምዕራብ ጎጃም ገበሬ ማህበር፡ የቁጥጥር፡ ኮሚቴ ሰብሣቢ፡ የነበሩትን፡ አቶ ገዳሙ በላይን፡ 4/ አሁንም፡ በምዕራብ ጎጃም በዳጉሣ ወንበርማ ወረዳ፡ የወገዳድ ዮህንሥ፡ ገበሬዎች፡ የአምራቾች፡ የህብረት ሥራ ማህበር ሊ/ መንበር የነበሩትን፡ አቶ ታደሰ ምናሉን፡ ማሥታዎሱ፡ ብቻ በቂ ነው:: ይህንን ስል ወያኔን በቅርበት፡ የማያውቅ፡ አንባቢ፡ እንዴት  እንዲህ አይነት፡ የጭካኔ ሥራ ይከናወናል፣ በምን : መንፈስና ህሌና ቢታዘዙ ነው፡ የሚሉ ጥያቄዎች፡ በሰልፍ፡ ሊመጡበት ይችላሉ፡ መልሱ እነዚህ ሰዎች፡ ህሌና የሚባል ነገር፡ አልፈጠረባቸውም፡ መንፈሱ ግን : በአሸሸ የሚታዘዝ፡ እርኩሥ መንፈሥ ነው፡ የሰፈረባቸው፡ የሚለው፡ ይሆናል። ለምሣሌ ጠቅላይ ሚነስተሩ፡ በአንድ ወቅት፡ ካፓላ ላይ ስብሰባ፡ እንደተቀመጡ፡ የመጠቀሚያ፡ ጊዜያቸው በማለፉ፡ አዙሮአቸው፡ ሥለወደቁ፡ የስብሰባው፡ ተካፋዩች ተደናግጠው፡ በማንሣት፡ ተጠራጥረው፡ ኪሣቸውን፡ ሲፈትሹ፡ አጅሪን አገኙና፡ የምሣቸውን ሰጥተው፡ ነፍሣቸውን ግዝተውላቸዋል ይባላል፡ የሌሎች በጠቅላላ፡ የደም ሥራቸው የሚሥራ፡ በእሱ ሥለሆነ፡ ተከድኖ ይብሰል፡ ብሎ ማለፉ ይሻላል።

ወደመነሻየ፡ ልመለሥና፡ እውነቱን ለመናገር፡ ሪፖርተር ጋዜጣ፡ በዋቢነት የጠቀሰው፡ የሕዝብ ቆጠራ ሃላፊዋ፡ እሪፖርት፡ ተደብቆ የኖረውንና፡ በአማራው ህዝብ ላይ፡ ለ18 አመታት፡ እየደረሰ ያለውን፡ ዕልቂትና፡ ፍልሰት፡ በመጠኑም ቢሆን ያጋለጠ፡ ቢሆንም፡ የሞተውንና የተሰደደውን ህዝብ ቁጥር፡ ግን በጣም፡ ያሣነሰ ነው:: ምክናያቱም፡ ታላቂቷን ትግራይን : በቆዳስፋትም፣ በህዝብ ብዛትም፡ ለመገንባት፡ ሲባል ከወሎና ከጎንደር፡ ተቆርጦ ያለውዴታው፡ ትግሪ ነህ የተባለውንና፡ ቤት ንብርቱን፣ አጽመ እርሥቱን፣ እየተዘረፈ፡ በሀገሩ ላይ ሰርቶ የመኖር፡ መብቱን እየተገፈፈ፡ የተሰደደውን፡ የአማራ ክልል ህዝብ፡ ሣንጨምር፡ ከላይ ለመጠቃቀሥ፡ በሞከርኳቸው፡

የወያኔ የረቀቀ፡ የዘር ማጽዳት(ማጥፋት)ዘመቻ በኢትዮጵያ፡ አይድለም፡ በየትኛውም፡ ዓለም ታይቶና ተሰምቶ በማያውቅ፡ አሰቃቂ፡ ሁኔታ ያለቀው፡ የአማራ ህዝብ፡ በትክክል ቢቆጠር፡ ያለጥርጥር፡ ከ4.5 እስከ 5 ሚሊየን፡ ይደርሣል፡ ባይነ ነኝ። መቸና፡ እንዴት በሀቅ ተቆጥሮ፡ ያለቀው ወገናችን፡ ይታወቃል? ወደፊትስ እንዴት ዘራችንን ከመጥፋት እናድናለን? የሚሉ ጥያቄዎች፡ በሕሌናው ጓዳ የሚያቃጭል፡ አንባቢ፡ እንደማይጠፋ፡ እግምታለሁ፡ ለእነዚህ፡ መሰረታዊ ጥያቄዎች፡ መልስ ይሆናል፡ ብየ የምገምተውን፡ የግል፡  አስተያይቴን፡ ከማስፈሬ፡ በፊት፡ የሁለት ጓደኛሞችን፡ የጉዞ ታሪክ፡ ቀልድ ባነሣ፡ ዛሪ እየሆን ያለነውን፡ የሚገልጸው፡ ይመስለኛልና፡ እንካችሁ፡ (ከህለታት አንድ ቀን፡ ሁለት ጓደኛሞች፡ የእሩቅ ሀገር ጉዞ ይጀምሩና፡ ሲመሽባቸው፡ ጫካ ውስጥ ይተኛሉ አሉ፡ ሌሊት ጅብ ይመጣና፡ አንደኛውን፡ መብላት ሲጀምር፡ ተበይው ሥቃዩን ችሎ፡  እንደአሁኑ፡ እንደ አማራው ፡ ህዝብ፡ ተበልቶ እስከሚያልቅ፡ ዝም፡ በማለት፡ ሲጠብቅ፡ ከጎኑ የተኛው፡ ይነቃና፡ የምን ድምጽ ነው የምሰማው፡ ቢለው፡ ዝምበል የእኔን እግር፡ ጅብ እየበላው ነው አለው ይባላል) ነገሩ እውነት፡ ሆነም አልሆንም፡ በአጠቃላይ፡ የኢትዮጵያ፡ ህዝብ በተለይም፡ የአማረኛ፡ ተናጋሬው፡ ይህ ሁሉ የግፍ፡ አዝመራ፡ እየተወቃበት፡ ዝምታን፡ መምረጡ፡ በፍርሃት ገመድ፡ ታብቶ፡  በጅብ ከተበላው ሰው የተለየ አለመሆኑን፡ በምሣሌ የሚያስረዳ፡ ይመሥለኛል። እና ይህ ዝምታ፡ መቀጠል ያለበት፡ እስከመቸ ነው? የወያኔ ዕቅድ፡ ተግባራዊ፡ ሆኖ የአማራው፡ ዘር ከምድረ ኢትዩጵያ፡ እስኪጠፋ? እንደእኔ፤ እንደእኔ፡ ሞታችንን፡ ቆመን የምናሥተናግድ፡ አዘንተኛ እነታችን፡ ማብቃት አለበት፡ ቢያንሥ ዘራችንን፡ ከነበር፡ ታሪክ ማዳን የግድ ነውና፡፡ ለመሆኑ፡ እነሱ እነማን ናቸው? እኛሥ? ማንነን? በምንድን ነው የሚበልጡን? በምንሥ ነው የምናንሣቸው? ነው አቶመለስ እንዳሉት፡ እነሱ ከወርቅ፡ እኛከፋንድያ፡ ተሰርተናል፡ ብለን እራሣችንን፡ አሣምነናል? የእነሱን፡ እርካሽ፤ ስንኩልና፡ ጠባብ አላማ፡ እንደማራመድ፡ አይቆጠርብኝና፡ ሌላውን ኢትዮጵያዊ፡ ወገናችንን፡ ሣይጨምር፡ አማራው፡ ብቻውን፡ ቢገጥማቸው፡ ለስአት እንኳን፡ መመከት፡ ይችላሉን? ታዲያ ከዚህ የከፋ፤ የከረፋ ምን እስኪመጣ ነው፡ የምንጠብቀው? ማንስ መጥቶ ከዕልቂት፡ እንዲታደገን ነው፡ የምንጠብቀው? ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም፡ ይባላል፡ ከቆረጥን፡ እኛው ከበቂ በላይ፡ ነን እንጅ፡ ሌላ ሃይል፡ የምንሻ ቢሆን እንኳን፡ ሣንጀምረው፡ ሊመጣልን የሚችል፡ አይኖርም። እየተከላከልን፡ ሌላው ኢትዩጵያዊ፡ ወገናችን፡ እንዲያግዘን፡ መጠየቅም የወግ ነው፡ ዝምብሎ ከማለቅ።

ሁሉም፡ እንደሚያውቀው፡ ይህ መሰሪ፡ ቡድን የሀገሬቷን፡ በትረሥልጣን፡ ከጨበጠበት፡ ጊዜ ጀምሮ ቁልፍ፡ ሥራው፡ ያደረገው፡ ተዋዶ፤ ተጋብቶ፤ ተዋልዶ፡ የኖረውን፡ የኢትዮጵያን፡ ህዝብ፡ ያልነበር፤ የሌለና፤ እሱ ከተወገደ፡ በኋላም፡ የማይኖር፡ ሥምና መልክ፡ በመሥጥት፡ ከፋፍሎ፡ እርስበርስ፡ በማናከሥ፡  አናጥሎ፡ መፍጀትን ነው። እድሜ፡ ለአረመኔው፡ ተላላኪው፡ ለታምራት፡ ላይኔ፡ ውሎ ሣያድር፡ ሕልሙ እውን ሆኖ፡ ዓላማው፡ መሣካት፡ የጀመረው፡ በኦሮሞውና፡ በአማራው፡ ሕዝብ መካከል፡ የተዘራው፡ መርዝ አፍርቶ፡ በአርባ ጉጉ፤ በበደኖ፤ በአሰቦት፤ በአሶሣ፡ ወ. ዘ . ተ.ነበር፡ ምርቱን፡ ያፈሰው፡ እየቆየ፡ ተሥፋፍቶ፡ ዛሪ  ከትግራይ፡ ክልል በቀር፡ በመላው ሀገሪቷ፡ ፍጅቱ ቀጥሏል፡ ያማራው፡ ላቅ ብሎ ይታይ እንጅ። አዎ! በዚህ፡ ወያኔ ሰራሹ፡ እራብ፤ እርዛት፤ በሽታ፤ ጦርነት፤ እንደቅጠል ያረግፈናል፡ በዚህ፡ የተጠመደልንን፡ ፈንጅ፡ እየረገጥን፡ እርስ በእርስ፡ እንፋጃለን፡ ከዚህ የተረፍን፡ ብንኖር፡ ደግሞ፡ ትልቁ፡ ጠላት፡ ከፊታችን፡ ተገትሮልን፡ እያለ እሱን ትተን፡ ከፍሲል፡ በብሄረሰብ፡ ዝቅ ሲል በድርጅት፡ ሲወርድ ደግሞ፡ በጥቅምና፡ በመንደር፡ እየተቧደን፡ እኛው፤ በ እኛው፡ ሥንነታረክ፡ የወያኔን፡ ዕድሜ ከሚገባው፡ በላይ እያራዘምነው ነው፡ ብቻ ሣይሆን፡ ሁልጊዜ፡ የምለውን፡ ዛሬም ልድገመውና፡ ኢትዮጵያ፡ የምትባል፡ ሃገር ከዓለም፡ ካርታ እንድትፋቅና፡ ኢትዮጵያዊ፡ ነኝ በማለት አፍሞልቶ፡ ደረትነፍቶ፡ የሚናገር፡ ዜጋ እንዲጠፋ፡ የሚያደርገውን፡ ዘመቻ  እያፋጠንለት፡ ነው። እረጎበዝ፡ ምንይሻላል? ? ? ? ? ?።

ሞት ለወያኔ!!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!!

ሐምሌ2001